# ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?

ቁጥር 10

መታለሉ ቀርቶ ሁሉን ያታለለ
ብልኀ ሰው ይባላል በጣም የታደለ

ብለው አቶ ከበደ ሚካኤል በሽሙጥ የፃፉት ዛሬ የብዙዎች መመሪያ ሆኖ፣ የወያኔ መፈክር ሆኖ፣ ማታለል መዋሸት፣ መዋሸትና ማደናገር በስልጡንና ዘመናዊ ፖለቲካነት ተፈርጀው ሀቅን ሙጭጭ ብሎ የያዘው በኋላቀርነት ወይ ግትርነት ወይ ከተሜዎቹ እንደሚሉት በፋራነት ተመዳ ቢ ሆኗል።

ካሳቡ አፍልቆ በውሸት ፈጠራ
ያልሆነውን ነገር ቃኝቶ የሚያወራ
መስለህ ትታያለህ ሰክሮ ዘባራቂ
አትመስልም ነገሩን አጥርተህ አዋቂ.....

ሲሉም አቶ ከበደ በትንቢት ቀጠሮ ያሰፈሩት ዛሬ ብዙዎችን ገላጭ ሆኖም ይገኛል። ዋሾዎቹ ለመዋሸት መስከርም የለባቸው ምንም እንኳን በየማታው በሼራተንና በብልግና መሸታ ቤቶች የሚፈሰው ውድ ውስኪና ኮኛክ ከመ ኅርፍ ሊሆን ቢቃጣውም። የመለስ ቡድንና ሌሎች ወንጀለ ኞች መዋሸት የግድ ሆኖባቸው ሲገኝ ሌሎች ደግሞ ዘመን አልፎ ሲያበቃ ወደ ፖለቲካ ብቅ ብለ ው በዚያው ፍጥነት ፍየል ከመድረሷ ዓይነት ሆኖባቸው ሌሎችን አፍ ሊያስይዙ፣ ሊያቀሉና ከቻ ሉም ቦታ ሊያስለቅቁ ፈላጊ ናቸውና በተለይ በትግል በቆየው ኢሕአፓ ላይ የሀሰትና ውሸት ናዳ እንደ መርግ ማውረዱ ይቀናቸዋል። ኢሕአፓን መዝለፍና መክሰስ ደግሞ በወያኔ መዘገብ ነጥብ ያስገኛልና አደርባዮቹ ለሆዳቸው ከበሮ ጆሮ ሲሰጡ አፋቸው/ምላሳቸው በኢሕአፓ ላይ መንጣጣ ቱ የግድ ይሆናል። የአንድ ተቃዋሚ ድርጅት መሪ ለምሳሌ ስለ ወያኔ አገዛዝ ኢዴሞክራሲያዊነ ት ያወቀው ወያኔ 14 ዓመት ገዝቶ ካበቃ በኋላ በ1997 መሆኑን ራሱ በፃፈው መፅሀፍ አሳውቆና ል። ሌላ በየሳምንቱ በባዕድ ቋንቋ ፅሁፉ ሊያነቃን የሚሰብከን ደግሞ እውነቱን ለመናገር ወደ ፖለቲካ ብቅ ያልኩት በ1997 ነው ብሎ ነግሮናል። ወደ ፖለቲካ መምጫቸው ወይ መንቃታቸ ው መዘግየቱ ሳይሆን ችግሩ፣ ከመቸው እንዲሉ የቀዩትንና ሲታገሉ የባጁትን ለመተቸትና ለመ ውረፍ መቸኮላቸው ነው አነጋጋሪ እየሆነ ያለው። ትሁት ሆኖ መማር፣ የሀገርን ተጨባጭ ሁኔታ ለማወቅ መጣር ያስፈልጋል የምንለውም ለዚህ ነው። አንዳንዶች ዛሬም ወዳጅና ጠላት ማን እን ደሆነ ገና ማወቅ ተስኗቸዋል። ህብረት ሲሉም ከማን ጋር መሆን እንዳለበት ከቶም አልረዳ ብሏቸ ው አፍቅሮ ወያኔ የሚወዘውዘውን ሽፍንፍን ተለጣፊ ወይም ሀገር ሊገነጥል የሚለውንም ሊያቅፉ ደፋ ቀና ይላሉ። በውጭ ደረጃም መዳካማቸው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አስፈላጊ የሆነውን ሀገሮች ጥንካሬ ወይም አንድነት ይመኛሉ። በዚህ ሁሉ አቅጣጫ ኢሕአፓ ስህተታቸውን ሲያርም ና ሲተች በግትርነትና በአክራሪነት ይከሱታል፣ ይህን ለማሳመንም ሀሰትና የፈጠራ ወሬን ይሰዱ በታል።

ኢሕአፓን በግትርነትና በአክራሪነት የሚከሱትና በዚህም ረገድ ብዙ ውሸቶችን የሚያሰራጩበት በመሰረቱ ችግራቸው የወገንተኛነትን ወሳኝነትና አስፈላጊነት መረዳት ያቃታቸው መሆናቸው ነው። ከአንድ ፅንፍ ወደ ሌላ ሲስፈነጠሩ ኢሕአፓን ባለበት አውግዘው ያልፉትና ከሄዱበት ፅንፍ ደግሞ ያሰቡት አልሆን ብሎ፣ ሊበሉ የተመኙት ጠፍቶ፣ ሊያድሩለት የፈለጉት ጌታ ወግዱ ብሏቸው ወደ ሌላ ፅንፍ ሲወረወሩ ኢሕአፓ ባለበት ፀንቶ ሲያገኙት ያው በግትርነት ያወግዙታል ። አቅዋምን እንደ ሀብታም ሸሚዝ በፈጣኑ እየቀያየሩና መርህ ብለው አጥብቀውና አምርረው የሚይዙት ከቶም ቅንጣትም ነገር ባለመኖሩ (ሁሉም ለገበያ የሚቀርብ በመሆኑ) መርሁን አጥብ ቆ የያዘውን ኢሕአፓን ግትርና አክራሪ ይሉታል። አቅዋሙን አላስማማ አልሸጥ ያለውን ግትር ማለቱ ይቀናቸዋል። ከመርህ በመለስ ግን ኢሕአፓም ቢሆን የሁኔታዎችን ለውጥ እያየ፣ የሕዝብ ን የልብ ትርታና ፍላጎት እያዳመጠ፣ የሀገርና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ለውጥም እያገናዘበ አቅዋሙን ያስተካክላል። በመጀመሪያ መርህ ግብሩ ወይም ፕሮግራሙ ለምሳሌ መሬት መታገር አለበት የሚል አቅዋም ይዞ የነበር ሲሆን የደርግን የማገድ ተመክሮ ክስረትና ከሕዝብም ፍላጎት መፃረር በተገነዘበ ጊዜ በሁለተኛ ጉባዔው (ቋራ 1976) ይህን ሰርዞ መሬት ለአራሹ በባለቤትነት መቆየቱን ደግፏል። በኤኮኖሚው መስክም ቅይጥ ኤኮኖሚን ሲያስቀድም በብሄረሰብ ጥያቄ ረገድ ደግሞ ግልፅ ባለ መንገድ የግንጠላን ጎጂነት አስረግጦ እኩልነትን ማስፈንና አንድነትን በዴሞክራሲ ማጀብ ቀዳሚነቱን ሲገልፅ ለኤርትራ ችግር ደግሞ ሲለው የቆየውን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መፍትሄ ዘርዘር በማድረግ የፌዴሬሽን አማራጭን አቅርቦ ነበር። ወያኔ ከመሸ ነቅቶ የአልባኒያ ሶሻሊዝም ወይም የስታሊን አፋኝ ስርዓትና መንገድ ተከታይ ነኝ ብሎ ሲለፍፍ ኢሕአፓ ይህን ከማውገዙ ባሻገር በማያወላዳ ደረጃ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት መመስረትአለበት ብሎ አቅዋም ይዟል። ይህ ሁሉ በወቅቱ በሰነድ ሰፍሮ በይፋ የቀረበ በመሆኑ ለዋሾዎች ቀዳዳ አይሰጥም።

ኢሕአፓ ድርጅታዊ መንፈስ የሚንፀባረቅበት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በዚያው መሰረት ወገንተኛ ድርጅት ነው። የሚታገለው ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ነው። በቅድሚያ ለሰርቶ አደሩ ሕዝብ ማለት ነው። ወገንተኛነቱ በዚህ ይገለጣል። ለጭቁኖች ጠበቃና ተከራካሪ ነው። በአፍሪካና ዓለም አቀፍ ደረጃ ስልፉ መቸም ቢሆን ከጨቋኞች ጋር አይደለም። በዚህ መልክ ሰልፉን ከለየ ዓመታት አልፈዋልና ከሰልፉ ዝንፍ ብሎ አይወጣም፣አልወጣምም። ለጭቁ ኖች መብትና ለሀገር ሉዓላዊነት ግትር ድርቅ ብሎ ይታገላል። የሚደራደረው የለም--መነሻው መሰረቱ ለድርድር የሚቀርብ አይደለምና። በመሆኑም ሀገራችንን ሊቀራመቱ ለሚፈልጉ ባዕዳን ኢሕአፓ ተመችቷቸው አያውቅም። አይለሳለስላቸውም። ሱዳንም፣ ቻይናም፣ ሶማሊያም ሆኑ ምዕራባውያን ኢሕአፓ በሚፈልጉት መንገድ እንዲቆምላቸው በፈለጉ ጊዜ ሁሉንም አምቢታውን አቅምሷቸዋል። ለሀገር ከማይጠቅሙ ባዕዳን ኢሕአፓ እንኳን ኩርኩም ምክርም እንደማይቀበል በተመክሮ የተረጋገጠ ነው። በተጨማሪ ታክቲክ ወይ ዘዴና አድርባይነትና መርህን መቸብቸብ የተለያዩ ናቸው። ማታለል መዋሸት ብልህነት አይደለም፣ መርህን መሸጥ ብልጥነት ሊሆንም

አይችል። ደርግም ወያኔም በሹመትና ጥቅማ ጥቅም ሊደልሉት ሲሞክሩም ብልጥ ሆንኩ በሚል ሽፋን አልተገዛላቸውም። ይህ ፅኑ የኢሕአፓ አቅዋም የሚያስከፍለው ዋጋ ቀላል አለመሆኑን ከሁሉም በላይ የሚያውቀው ገፈት ቀማሹ ኢሕአፓ ራሱ ነው። ግን ሁኔታው ከፋ ብሎ ለጠላት መንጋ መጎንበስን አልመረጠም። እየለፈለፈስንት ሊቅ ተጎዳ እንደተባለው በአሁኑ ጊዜ ከወደ ልፍለፋው ጠበቅ እያደረጉ ያሉ ክፍሎች ከወደ መርሁ ለቀቅ ማድረጋቸው እየታየ ነው። ፅናትና ወገንተኛነት ከማነሱ ወይም ጭራሽ ድራሹ ከመጥፋቱ ሌላ ሰፊውን ሕዝብ የመናቅ አባዜም ተስፋፍቶ ለማን ሊታገሉና ማንን ሊታገሉ ተነሳን እንዳሉ ግልፅ ያልሆነበት ሁኔታ ሰፍኖ ይገኛል። ኢሕአፓዎች ወገንተኛነታቸው ያልተለወጠና ያልቀነሰ በመሆኑ-- ( ስንቱ ከወያኔ ጋር እበላ ብሎ የጎጠኛ ጉዞን የተጓዘ እስቲ አሌ ይበለን!)---ድርጅታቸው የዚህ ሀገራው ትግላቸው መሳሪያ በመሆኑ ያፈቅሩታል።የዚህ ይዘቱና ምስጢሩ ያልገባቸው ደግሞ የኢሕአፓ አባላት ድርጅታቸውን ከሀገር ያስቀድማሉ ብለው አላዋቂነታቸውን ያጋልጣሉ። ከሀገርና ከሕዝብ በፊት ማን ሊቀድም?!

ሀገር አቅኚ ይባል እንደነበረው ዛሬ ደግሞ ሀገር ጎብኚ ወይም ቱሪስት የሚባል ፍጡር አለ ። ይህ ቱሪስት ከቦታ ቦታ ጎብኚ ሆኖ እንደሚዞረው ሁሉ የድርጅት ቱሪስቶችም ተፈጥረዋል። ከድርጅት ድርጅት የሚዞሩ፤አቅዋም የሚቀያይሩና ይህንንም መሰልጠን ማወቅ ነው ብለው የሚያቀርቡ። እነዚህ ፍጡሮችም በኢሕአፓ ለይ ክስና ውሸት ከሚደረድሩት ክፍሎች አንዱ ናቸው። በየጊዜው ከድርጅት ወደ ድርጅት መሸጋጋሩና አቅዋምንም በዚያው መቀያየሩ ብልህነት ሳይሆን መደናገርና አድር ባይነት ነው። ከዚህ ተያይዞም ራሳቸው ዘመናዊ ድርጅቶች ነን ባዮች ሀቅ ይነገር ከተባለ ድርጅት ለመሆናቸው በቂ ማስረጃ የለም። መሪውም ተመሪውም በጣት የሚቆጠሩ ሆነውና ለዓመታት ቁጥራቸው ሲያድግ ወይም እንቅስቃሴያቸው ሲጨምር አልታይ  ሲል ድርጅት ብሎ መጥራቱ ስህተት ይሆናል።  የድርጅትም ይዘት ስለሌላቸው መጠነኛ ችግርም ሲመጣ ፍርክስክስ ብለው ይተናሉ። ስፖርት ለፓስፖርት ይባል እንደነበረው ድርጅት ለገንዘብ ክምችት ሆኖ የሚታያቸው ጥቂቶች አይደሉም። ድርጅት የተባሉት የድርጅት ይዘትና ሙያተኛ ጠባይም የሌላቸው በመሆኑ ለስራ ተነሳን ሲሉ ውስጠ ምስጢራቸው በጠላት ታውቆ ወዲያውኑ ይመታሉ። ይህን መሰረታዊ ድክመታቸውን ከማስወገድ ፈንታ፤ ተደራጀን ሲሉ በራሳቸው ጥረት ሕዝብን ከማደራጀት ይልቅ ኢሕአፓን መክሰሱና ማጥላላቱን ይመርጣሉ። ኢሕአፓን ጎዳን ሲሉም በሂደት ብዙውን ዜጋ በትግል ላይ ተስፋ ያስቆርጣሉ--ግን አያድጉም፤ ከመጫጫትም አያመልጡም። ጉሙ ሲተንም እነሱ ሲተኑ ኢሕአፓ ግን ትግሉን ቀጥሎ እንደሚገኝ ደግሞ የታየና እየታየም ያለ ሀቅ ነው። ለዚህም ነው ኢሕአፓ ህብረትን እምቢ አለ ወይም ድርጅቶችን ናቀ ወዘተ ብለው ሲከሱ ውሸት የሚላቸው።  በህብረትም ተሰልፎ ቆይቷል። ተመክሮም ገብይቷል። አሁን ከያዘው የራስ ማጠናከር ስራ ወደ ህብረት ለመሸጋገር ግን ህልውና ካላቸው፤ በወያኔ ላይ ቁርጥ ያለ የጠላትነት አቅዋም ከያዙና የሀገር አንድነትን ከማይፃረሩ ጋር ለመወያያትና መንገድ ለመፈለግም ዝግጁነቱን ገልጿል። ያለፈውን ድክመት ላለመድገም፤ ሰኞ ከወያኔ ጨፍሮ እሁድ ተቃዋሚ ነኝ ከሚለው ላለመተቃቀፍና ላለመጎዳት፤ ድርጅት በሚልም ምንም አቅም፤ የሰው

ሀይል ወይም እንቅስቃሴ ኬሌላቸው ጋር ተያይዞ ላለመመዝበርና ተግባር አልባ ላለመሆን፡፡ ሀቁ ይህ ነው፡፡

ለኢሕአፓ ትግል የይስሙላ፤ የንግድ ወይም የጡረታ ጊዜ ስምሪት አይደለም፡፡ መከራ የሚቀበል በት፤ መስቀሉን የሚሸከምበት፤ የሚሳደድበት፤ ስየል የሚቀበልበትና ውድ ህይወቱን የሚገብርበ ት ነው፡፡ ሀገርና ሕዝብን፤ የነገ ዕጣቸውንም በሚዛን ያስቀመጠ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የመድረክ ጩኸትና ልፈፋ አይደለም፡፡ አዛውንቱ አብዮታዊ ብለውት እንደነበርም የራት ግብዣና አስረሽ ምቺው አይደለም፡፡ ትግል መራራ ነው--ምሬቱ የሚጠፋ ባይሆንም እንደ መራራ የኮሶ መድሀኒ ት በግድ የሚቻለው ግን ውጤቱ ከሰው በላ ትሎችና አረመኔ አገዛዞች ስለሚገላግለን ብቻ ነው፡፡ ኢሕአፓ ለሕዝብ ቆምኩ ወይም ቆሚያለሁ ሲልም ሁኔታው ሲጠጥር ሊከዳ ሳይሆን ጥርሱን ነክሶ ና መርሁን ጠብቆ ትግሉን ቀጣይ ነኝ ማለቱ ነው፡፡ በዚህም መስክ የምንለያቸው ስላሉ ነጋ ጠባ በውሸት ናዳ ሊቀብሩን መፈለጋቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ ትግል ከሁሉም በፊት ግን ተግባር ነው፡፡ ስለ ትግል ማውራት ሳይሆን በትግል መሰለፍና በትግል መሰማራት፡፡ ይህን በተመለከተም ሐሳዊ መሲሆችና አደናጋሪዎች ብቅ ባሉበት ኢሕአፓ ትግሉ እንዳይጎዳና አቅጣጫ እንዳይስት አለምን ም ለቀቅተኛነት ይታገላል፡፡ ለዚህም ነው በሰላማዊ ትግል ሽፋን የፀረ ወያኔውን ትግል ጥርሱን ሊሰባብሩ የተነሱትን ገና ሲነሱ የተቃወማቸውና የታገላቸው፡፡ ለዚህም ነው ገና ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በወያኔ ላይ ትጥቅ ትግልን ለማካሄድ ሲጥር የቆየውና በኢአግም አማካይነት መስዋዕትነ ት የከፈለው፡፡ ለዚህም ነው ሕዝብን የሚያደናግሩ፤ ተቃዋሚ መስለው ግን የወያኔ ተለጣፊ የሆኑ ትንም ገና ብቅ ሲሉ እባቦች ናቸው ብሎ ያጋለጠው፡፡ ኢሕአፓ ሌሎች ድርጅቶችን ፀረ ወያኔ አገዛዝ እስከሆኑ ድረስ በሕዝብ ጎራ መድቦ የሚንቀሳቀስና በተቻለውም ሊያግዝና ሊመክር-- ሊተባበር የሚጥር ድርጅት ነው፡፡ የተባሉት ድርጅቶች ከሕዝብ በስተጀርባ ሆነ ፊት ለፊትም ከወያኔ ጋር መመሳጠርና መሞዳሞድ ሲጀምሩም ኢሕአፓ በይፋ ተቃውሞውን አሰምቷል፡፡ ለዚህም ነው ከማንም በፊት ዛሬ እርቃናቸውን የወጡ ከሀዲዎችን ሆኑ አስታራቂ ሽማግሌዎች ነን ባዮች የመለስ መሳሪያዎችን ወዘተ በሕዝብ ፊት ያጋለጠው፡፡ ይህ ደግሞ ለኢሕአፓ ግዴታው ነውና ግዳጁን በመወጣቱ ይደሰታል እንጂ ድርጅቶችን ይተናኮሳል ብለው ስለሚዋሹ ተሸማቀ ዝም አይልም/አላለም፡፡ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ነን እያሉ፤ በድህነት እየተሰቃየ ያለ ሕዝ ባችንን ወካይ ነን ብለው እየቀረቡ እንደ ናጠጠ ከበርቴ በሀገር ቤትም በባዕድ ሀገርም ከሕዝብ የተሰበሰበ የድርጅት ገንዘብን በአልባሌ መንገድ በአደባባይ ወይም ባልሆነ ስምሪት ሲያባክኑ መውቀስ ፀረ ድርጅት ያሰኛል? የመለስን አገዛዝ ለመታገል ከተፈለገ ደግሞ ደርጅትም ትግልም በትርፍ ጊዜ ስራ ወይም ስምሪት ደረጃ ሊያዝ የሚችል አይደለም፡፡ የድርጅቱ በቂ መሪዎችና ዋና ተንቀሳቃሾች በሞያተኛነት መሰለፍ መቻል አለባቸው፡፡ ትግል እንደ ትርፍ ጊዜ ስራ፤ የጡረ ታ ስምሪት፤ መዝናኛ፤ ወዘተ ተደርጎ ከተወሰደ ጠላት ተዝንናንቶ ሊተኛ ይችላል፡፡ ኢሕአፓ ይህ ንን በመጠቆሙ ትግልን እንደ ጡረታ ስምሪትና አልፎ አልፎ ስራ የሚወስዱ --የወያኔንም አገዛ ዝ ጠባይና አሰራር ከቶም ያልተረዱ-- ይዘልፉታል፡፡

ኢሕአፓ ከማንም ቀድሞ በራሱ ግለሂስ ያደረግ ድርጅት ነውና አልሳሳትም ብሎ አያውቅም። ሁሌም ተመክሮውን እየገመገመም የተሳሳተውን ለማረም የሚጥር ከመሆኑ በላይ ሂስንም ጋባዥ ነው። ሂስ አይፈራም፤ መወቀስ መዋረድ ነው አይልም። በሕዝብ ላይ የበላይ ነኝ ብሎ ተኮፍሶ የከረመ ድርጅት አይደለምናም ማንም ዜጋ ሊወቅሰው መቻሉን ይቀበላል። ሂሱን ካልተቀበለ ደግሞ አልቀበልም የማለት መብቱንም ያስጠብቃል። ለዚህም ነው የዘነበበትን ውሸት ሁሉ ጊዜ ወስዶ የሚያጋልጠውና ሀቁን ለማስፈን እየጣረ ያለው። የኢሕአፓ አቅዋሞ በአመራር አባሎች ሳይሆን በአባላት በጉባዔ የሚወሰን ነው። ስለዚህ የደርጅቱ አሰራር ይህን መርህና ልምድ ያከበረ ና የጋራ አመራር መርህንም የተቀበለ ነው። የአመራር አባሎችም በሚገባ ተገምግመው በየጉባዔ ው ይመረጣሉ። በኢሕአፓ ውስጥ መለስም መንግስቱም ብቅ የሚሉበት ሁኔታ አልነበረም/የለም ም። አምባገነናዊ ዝንባሌ ያሳዩትን ደግሞ ሊያርም ሞክሮ  አልታረም ካሉ እንደሸኛቸውና መጥፎ ዝንባሌያቸውም የፖለቲካ ምድረበዳ እንደከተታቸው የታየ ነው። ኢሕአፓ ሁሉን አዋቂ ከሀሊ ፈፃሚ አድራጊ ግለሰብ ሊቀመንበር ወይም ፕሬዚዳንት ኖሮትም አያውቅ። ወደ ጣዖትነት ያዘነበሉ ግለሰቦችን በድርጅት ላይ ማስቀመጥ ፀረ ዴሞክራሲ ነውም ብሎ ያምናል። ስለዚህ በድ ርጅቱውስጥ ያለው ዴሞክራሲ ምንም እንኳን በሚያካሂደው ህቡዓዊ ትግል የሚወሰን ቢሆንም ለመጪው ስርዓት ነፃብራቅ መሆኑ አልቀረም። መሰረታዊ መርሆዎቹ--ስለ ዴሞክራሲ መብቶች አለገደብ መከበር ያለው አቅዋም፤ የአንድ ድርጅት አምባገነናዊ አገዛዝን በጥብቅ መቃወሙና ለመድብለ ፓርቲ መቆሙ፤ የብሄረሰብ፣የፆታ ወዘተ ልዩነትን መቃወሙ፤ ሀይማኖትና መንግሥት  መለየት አለባቸው የሚለው አቅዋሙ፤ በሀገር ሉዓላዊነትላይ ያለው የማያወላውል አቅዋም ወዘተ --ሁሉም የኢሕአፓን ማንነት ገላጭ ናቸው።  በመሆናቸውም ዋሾዎችን ያጋልጣሉ።

ኢሕአፓ በግማሹ አርበኛ በሌላው ግማሽ ደግሞ ባንዳ የሚል ፊሊጥ አያውቅም።  ግማሽ ዴሞክ ራት ግማሽ አምባገነንነትንም አያምንበትም። በመሆኑም ኢሕአፓ በመርሁና በአቅዋሙ እምነቱ ሙሉ ነው። በመርህ ደረጃ ወይ ነጭ ወይ ጥቁር የሚለውም በዚህ የተነሳ እንጂ በሰው ልጅ ህይወት ሂደት ያለውን ቢጫና ግራጫ አላይም ብሎ አይደለም። ዴሞክራሲያዊ ነን እያሉ፤ ለአዲስና ብሩህ ቀን እንታገላለን እያሉ በዚያው ደግሞ የጭቆና አዳናቂ መሆን የሚቻል አይደለ ም።  በብሄረሰብ ልዩነት የሚያምን፤ ዘረኛ የሆነ /ች፤ ሴቶችን ዝቅተኛ አድርጎ የሚወስድ፤ በሀይ ማኖት ልዩነት የሚያምን፤ ሚሊዮኑን ድሀ ሕዝብ የሚንቅና በምርጥነት ስሜት የሚወዘወዝ በኢሕአፓ ቦታ የለውም።  ይህ ማለት ግን ኢሕአፓ ውስጥ ይህን ዓይነትና ሌሎችም ድክመቶች ያሏቸው አባላት የሉም ማለት ሊሆን አይችልም። ድርጅቱ ግን ከተሳሳተ አቅዋማቸው እንዲላቀ ቁ አሊያም ድርጅቱን እንዲለቁ ያደርጋቸዋል። ለኢሕአፓ መርሆቹና መሰረታዊ አቅዋሞቹ የይስሙላ አይደሉም--የእምነት ጉዳይ ናቸው። ድርጅቱን ይገልፁታል፤ ከሌሎችም ይለዩታል። አባሎቹም በነዚሁ መርሆዎች ህይወታቸው የሚመራ የሚገለፅ ይሆናል ማለት ነው።  ድርጅት

ሲሉ፣ መርህ ስንል ከሌሎች የምንለየው በዚህ መንገድ ነው:: የሲቪክ ማህበራትን ነፃነት ኢሕአፓ ይቀበላል ሲባልም ይህነፃነት ለዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ መኖር ወሳኝና አስፈላጊ በመሆኑ ነው::በዋናው ትግል ሽፋን ውሁዳን ወይ ጭቁኖች ተደራጅተው እንዳይታገሉ የሚዘረጋውን ጋሬጣ ለማስወገድም ነው:: ስለዚህም ኢሕአፓ ሕዝብ በማህበራት፣ በሙያቸው፣ በፆታቸው ወዘተ መደ ራጀታቸው አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል:: ዋናው ተልዕኮ የወያኔን አገዛዝ መጣል አንጂ ለምሳሌ ሴቶች ለምን በራሳቸው በማህበር ይደራጃሉ የሚለውን ክርክር ደግመን ደጋግመን ያዳመጥነው ቢሆንም ስህተትነቱ አይቀየርም:: ከወዲሁ መራጀትና መብታቸውን ለማስከበር መዘጋጀት አለባ ቸው--የሴቶችን መብት እናስከብራለን ብለው ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ አቅዋማቸውን የሚቀይ ሩ ገዢ ክፍሎች ለመኖራቸው ሩቅ ሄደን አልጄሪያ ማለትም የለብንም--እነ መለስ ራሳቸው ምሳ ሌ ናቸውና:: ስልጣንን ባልያዘበት ወቅት በተለይ ንዑስ ከበርቴ ተብሎ የሚታወቀው የህብረተሰቡ ክፍል ዋና ዴሞክራሲያዊነትን አቀንቃኝ ሆኖ ለስልጣን ሲበቃ ግን ያለፈውን አምባ ገነናዊ አገዛዝ መስሎ መገኘቱ ተደጋግሞ የታየ ነው:: ስለዚህ ኢሕአፓ የመደራጀት መብትን አጥብቆ የሚደግፌው አለምክንያት አይደለም:: የሕዝብን ዴሞክራሲያዊ መብትንም የሀገርና የሕዝብ ዋና ፍላጎት አሁን ዕድገት ነው፣ እንጀራ ነው፣ ኤኮኖሚውን ማሳደግ ነው ወዘተ በሚሉ የተለመዱ ሽፋኖች ወይም ባህልና ሀይማኖትን በሽፋን በመጠቀም የሕዝብን ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊገድቡ የሚሞክሩትን ሁሉ ኢሕአፓ ተቃውሞአቸዋል:: ሀገራችን ድሀ ነችና ከሁለት ሶስት ፓርቲ ውጪ ሊኖራት አይገባም ብለው ፈላጭ ቆራጭነትን ሊያነግሱና የሕዝብን የመደራ ጀትና የመምረጥንም መብት በዚሁ ሊያግዱ የጣሩትንም፣ የሰበኩትንም እንዲሁ አቅዋማችሁ ፀረ መድብለ ፓርቲ፣ ፀረ ዴሞክራሲ ነው ሲል ቅዋሚውን አሰምቷቸዋል:: ብዙዎቹ ትችቱን በቀና ባለመውሰዳቸውና የመቆጣጠር ዓላማቸውን ድርጅቱ ስላጋለጠባቸው ከአናርኪሰት እስከ አፍራሽ ና ሌላም አጓጉል ክሶችን አውርደውበታል:: ኢሕአፓ ግን ሕዝባዊነቱን ማንም ሊሰርዝ እንደማይ ችል በማወቁ በጫጫታው አልተሸበረም::

መዋሸት መቅጠፍስ ምንድነው ጥፋቱ
እንዳይገለጥ ነው መጠንከር በብርቱ

የሚሉ ሀቀን አፋኞች በኢሕአፓ ላይ የነዙትን ውሸት በሞላ ጎደል አንስተን ሀቁ ምን እንደሆነ ለማያውቀው ሁሉ ለማስረዳት ሞክረናል:: የውሸቱ ዘመቻ ይቆማል የሚል ብዥታ የለንም:: ሆኖ ም ሙሉ ትኩረታችን የሕዝብን ጠላት በመታገል ላይ መሆኑ ከመቀጠል አይለወጥም:: የሀሰት ዘመቻው ግን ማደናገር የጀመረ ሲመስለን ግን መለስ ብለን ዋሾውን ከነውሸቱ ማጋለጣችንን እንቅጥልበታለን:: ሀቅን ማስፈንና ታሪክን ከበራዦችና ዋሾዎች ጥቃት መከላከል ራሱ የትግላች ን አንዱ ገፅታ ነው::

የመለስ ዜናዊ ፀረ ሕዝብ አገዛዝ በትግላችን ይወገዳል!
ሀቅ ወዳጹ ሕዝብ ድልን ይቀዳጃል!
እናቸንፋለን!!